# ልዑል እግዚአብሔር፡

## የዛሬ ኹለት ሺህ ሦስት ዓመት፥
## በታኅሣሥ አንድ ቀን፡
## ባለሚሉን መልአክ፡ ቅዱስ ገብርኤልን፡
## ወደቅድስቲቱ ኢትዮጵያዊት ድንግል ማርያም ልኮ፡

**"ወናሁ ትፀንሲ! ወትወልዲ ወልደ!**
**ወትሰምይዮ ስሞ ኢየሱስ!"**

ማለትም፡

**"እነሆ ትፀንሻለሽ! ወንድ ልጅንም ትወልጃለሽ!**
**ስሙንም፡ 'ኢየሱስ' ትይዋለሽ!"**

ሲል በተናገረው አምላካዊ ቃሉ፡

# "ታላቁን፡ መለኮታዊና ዘለዓለማዊ ምሥራች!"

## ለፍጥረተ ዓለሙ ላሰማባት፥
## ለዚች፡ ለ፪ሺ፫(፳፻፫)ኛዋ
## የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ትስብእት፥
## (የፅንሰቱና የብሥራተ ገብርኤል በዓል)

እና

ታኅሣሥ ፯ ቀን ለሚውለው፡

## ለቅድስት ድንግል ማርያም የፅንሰቷ በዓል፡
## በያለንበት፡ እንኳን በደኅና አደረሰን!

---

# ስለ“ምሥራቹ!”

## ልዩ መግለጫና ማሳሰቢያ!

እስከ፪ሺህኛው የምሕረት ዘመን ድረስ በነበረው፡ በ፩ኛው “ሺህ ዓመት” ውስጥ፡ በጥልቁ፡ ተዘግቶበት ከቆየበት፡ የመለኮት እሥራት፡ ለጥቂት ጊዜ የተፈታው ዲያብሎስ፡ እነሆ፡ አኹን፡ በነጻነት እየሠራ እንደሚገኝ፡ በይፋ ይታወቃል፡፡

ከዚህ የተነሣ፡ ይህ “ምሥራች!” ዛሬ፡ ከኹለት ሺህ የምሕረት ዓመታት በኋላ፡ በዚህ፡ በ፪ሺህኛው ሦስተኛ ዓመት ላይ፡ እንደገና፡ እንደአዲስ፡ ሊቀርብና ሊገለጽ፥ ሊነገርና ሊደመጥ፥ ሊጻፍና ሊነበብ፡ እጅግ አስፈላጊ ኾኗል፡፡

አዎን! ይኸው “ምሥራች!” በአካሉና በባሕርዩ፥ በግብሩና በፍሬያማነቱ፡ የማይለወጥ፡ ያው አንዱ፡ ራሱ፥ የጥንቱና የመሠረቱ ቢኾንም፡ ዛሬ፡ የሚቀርብበትና የሚገለጽበት መልክና ይዘት፡ በቀደመው ዓይነት ሊኾን አይችልም፡፡ እንደዚያ ሊኾን የማይችልበት ምክንያት፡ ያ፡ የቀደመው “ምሥራች!”፡ የተነገረውና የተደመጠው፥ ኋላም፡ የተጻፈውና የተነበበው፡ የክፋቱ ኃይል፡ በእሥራት ተግዞ በነበረበት ዘመን ሲኾን፥ ይኸኛው፡ የዛሬው “ምሥራች!” ግን፡ የሚነገረውና የሚደመጠው፥ ከዚያም፡ የሚጻፈውና የሚነበበው፡ ይኸው፡ የክፋቱ አበጋዝ፡ እንደመለኮታዊው ቃል፡ ከእሥራቱ በተፈታበት ጊዜ በመኾኑ ነው፡፡

ስለዚህ፡ የዛሬው “ምሥራች!” አቀራረብና አገላለጽ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ሰፍኖ ከሚታየው፡ ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያውያን፥ ከመላው ሰብአዊ ኅብረተሰብና ከፍጥረተ ዓለሙ ኹኔታና ይዞታ አንጻር፡ ያለውን ትክክለኛ አግባብነት በማሳየት ይኾናል፡፡

እንግዴህ፡ ይህንኑ፡ የዛሬውን “ምሥራች!”፡ ከዚህ አስቀድመን፡ በኀዋ ሰሌዳችን ዋና ገጽ ላይ፥ በመጽሓፍም አትመን ባወጣነው ልዩ መልእክት፡ ገላልጸንና አብራርተን አቅርበነዋልና፡ አኹንም፡ በዚያው፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን መንፈስ ኾናችሁ፡ በአትኵሮትና በማስተዋል እንድትመለከቱት ጋብዘናችኋል፡፡

\+ \+ \+

## ታኅሣሥ ፩ ቀን፡

## የጌታችን፡ የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ትስብእት፤

## ብሥራተ ገብርኤል፤

## ታኅሣሥ ፯ ቀን ከሚውለው፡
## ቅድስት ድንግል ማርያም ከተፀነሰችበት ቀን መታሰቢያ ጋር፡
## በታላቅ ሓሤትና በእኩለ ሌሊት በሚፈጸም ቅዳሴ
## የሚከበርበት ሥርዓተ ጸሎት፡፡

---

<u>ምንባብ፡-</u>

ገላ. ምዕ. ፬÷ ቁ. ፩-፯፤
፩ኛ ዮሐ. ምዕ. ፬÷ ቁ. ፯-፲፩፤
ሐዋ. ምዕ. ፲፫÷ ቁ. ፲፮-፳፫፡፡

<u>ምስባ ክ፡-</u>

መዝ. ፻፴፩÷ ቁ. ፲፫-፲፬፤

እስመ ኃረያ እግዚአብሔር ለጽዮን፤
ወአብደራ፡ ከመ ትኩኖ ማኅደሮ፤
ዛቲ ይእቲ፡ ምዕራፍየ ለዓለም፡፡

እግዚአብሔር ጽዮንን መርጧታልና፤
ማደሪያውም፡ ትኾነው ዘንድ ወዷታልና፤
"ይህች፡ ለዘለዓለም ማረፊያዬ ናት!" አለ፡፡

<u>ወንጌል፡-</u>

ሉቃ. ምዕ. ፩÷ ቁ. ፳፮-፴፰፡፡

<u>ፍሬ ቅዳሴ</u>

ቅዳሴ ማርያም፡፡

## <u>የበዓለ-ትስብእት አጭር ዝማሬ</u>

አማን፡ በአማን፡ አማን፡ በአማን! (፪ ጊዜያት)
መንክር፡ ስብሓተ ትስብእቱ! (፪ ጊዜያት)

<u>ትርጉም</u>

እውነት በእውነት! እውነት በእውነት ! (፪ ጊዜያት)
መለኮት ሰው የመኾኑ ቸርነት፡ ዕፁብ ድንቅ ነው! (፪ ጊዜያት)

# <u>የምሥራች ሰላምታ</u>

በዚህ በዓልና ከዚህ ቀን ጀምሮ፡ እስከ በዓለ አስተርእዮቱ ድረስ፡ ካህናትና ምእመናን፥
እርስ በርሳቸው፡ የሚለዋወጡት የምሥራች ቃል፡-

**“ተፈጸመ ትስብእት፡ በማርያም ድንግል!"**

“በብሥራተ ገብርኤል፡ **ዜናዌ ቃል**! ”

**“የመለኮት ሰው መኾን፡ ተፈጸመ በማርያም ድንግል!" “**
**በአብሣሪው ገብርኤል፡ የምሥራች ቃል**!”

---

ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ከሚውለው፡ ከ“በዓለ ትስብእት” ተነሥቶ፡ ታኅሣሥ ፳፪ ቀን በሚውለው፡ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የፅንሰት በዓል በኩል አልፎ፡ እስከበዓለ ጥምቀት ድረስ ባሉት ወርና ሳምንታት ውስጥ የሚከበሩት በዓላት፡ በዚሁ ውስጥ ተካትተዋል፡፡ ይህም፡ ኅዳር ፲፭ ተጀምሮ፡ ኅዳር ፵፫ ቀን የሚያልቀው፡ “ጾመ ነቢያት”፡ <u>ታኅሣሥ ፳፱ ቀን</u> በሚውለው፡ በታላቁ፡ የፈጣሪያችንና የአምላካችን፥ የካህን ሊቀ ካህናታችንና የንጉሥ ንጉሠ ነገሥታችን፡ የኢየሱስ ክርስቶስ “ዕለተ ትስብእት” በዓል፡ በሓሤት ስሜትና በፋሲካ ደረጃ ከተከበረ በኋላ፡ ወዲያው፡ ታኅሣሥ ፴ ቀን፡ የ“ጾመ ማርያም” መዋዕል ይቀጥልና፡ “ከተራ” በሚባለው፡ ጥር ፲ ቀን በሚውለው፡ የጥምቀት ዋዜማ የሚያበቃው ነው፡፡

## ዕለተ ትስብእት፡፡

“ትስብእት”፡ “ቃል ሥጋ ኾነ!” ወይም፡ “'ቃል' የተባለው፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ሰው ኾነ!” ማለት ነው፤ ትስብእት፡ እግዚአብሔር፡ ሰው የመኾኑ ትንቢት የተፈጸመበት፥ ምሥጢሩም የተገለጸበት የመለኮት፡ ዕፁብ ድንቅ ሥራ ነው፤ ባጭሩ፡ የ“‘ምሥጢረ ሥጋዌ’ ሌላው ስሙና ገጽታው ነው!” ሊባል ይቻላል፡፡ የ“<u>ትስብእት</u>” ትርጉም፡ እንዲህ በሚል፡ በአንድ ዐረፍተ ነገር ይጠቃለላል፡- ኢትዮጵያዊቷ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ያለሰብአዊ ወንድ ዘር፡ በድንግልናዋ፡ በሰውነት የወለደችው እግዚአብሔር ወልድ፥ እርሱም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ በምሥጢረ ተዋሕዶ፡ <u>“ከኹለት አካላት፡”</u> ማለትም፡ <u>“ከመለኮትና ከሰውነት አካላት፡ አንድ አካል፥ ከኹለት ባሕርያት፡”</u> ማለትም፡ <u>“ከመለኮትና ከሰውነት ባሕርያት፡ አንድ ባሕርይ ኾነ!”</u> ማለት ነው፡፡

በእውነተኛውና በትክክለኛው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን ሥርዓት፡ ታኅሣሥ ፳ ቀን የሚውለው "ዕለተ ትስብእት"፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል የምሥራች ቃል፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የፀነሰችባት ዕለት ናት፡፡ በዚች ዕለት፡ እግዚአብሔር፡ በመልኩ ለፈጠረው የሰው ዘር ያዘጋጀው፡ ይህ ታላቅ ቸርነቱ ይፈጸምባት ዘንድ ወድዶ፥ በነፍሷም በሥጋዋም፡ ራስዋን፡ ለዚህ ፍጹም የንጽሕና ክብር አብቅታ ስለተገኘች፡ በመረጣት ቅድስት ድንግል ዘንድ፡ የኾነውንና የተደረገውን ድንቅ ነገር፡ ዝክረ ነገሩ፡ ሲወርድ ሲዋረድ በደረሰን፡ እንዲህ በሚለው የትውፊት ቃል እንጀምርላችኋለን፡-

"**ናሁ፡ ድንግል ትፀንስ! ወትወልድ ወልደ!**" ማለትም፡ "**እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች! ወንድ ልጅንም ትወልዳለች!**" ተብሎ፡ በነቢያት የተነገረው ትንቢት የሚፈጸምበት ጊዜ ሲደርስ፥ ማለትም፡ የ፭ሺ፭፻ ዓመተ ኵነኔ ዘመን ሲፈጸም፡ እመቤታችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ "ውኃ ስትቀዳ" ይላል፥ "በቤተ ዮሴፍ"ም ይላል፥ "በቤተ መቅደስ"ም ይላል፡ የእግዚአብሔር መልአክ፡ "**ትፀንሲ!**" "**ትፀንሻለሽ!**" አላት፡፡

"ይህ፡ እንደምን ነው?" ቢሉ፡ ኹሉም ተደርጓል፡፡ ከእስራኤል ደናግል ጋራ ውኃ ልትቀዳ ኼዳ፡ ስትመለስ፡ የተጠማ ውሻ ስላገኘች፡ ከቀዳችው ውኃ፡ ጨልፋ፡ በጫማዋ አጠጥታዋለች፤ "ርኅርኅተ ልብ" ያሰኛት፡ አንዱ ምግባርዋ፡ ይህ ነው፡፡ በዚህ ጊዜም፡ አብረዋት ከነበሩት ደናግል መካከል፡ አንዳንዶቹ "እኅቴ! ይህን ያህል ርኅራኄ እንዴት ነው? 'በዚህ ወራት፡ አምላክ፡ ከድንግል ይወለዳል!' ይባላል፤ ከአንቺ ይኾን?" አሏት፡፡ ወዲያው፡ መልአኩ ተገልጦ፡ "ትፀንሲ!" ማለትም፡ "ትፀንሻለሽ!" አላት፡፡ ዝም ብላ ኼደች፡፡ ከቤት ደርሳ፡ ውኃውን ስታወርድ፡ መልአኩ፡ እንደገና፡ "ትፀንሲ!" ማለትም፡ "ትፀንሻለሽ!" አላት፡፡ "ይህ ነገር፡ ደጋገመኝ! እስኪ፡ ከቤተ መቅደስ ኼጄ፡ ልረዳው!" ብላ፡ ከእስራኤል ደናግል ጋራ ተካፍላ፡ እያስማማች የምትፈትለው፡ ሐርና ወርቅ ነበር፤ ያን ይዛ፡ ወደቤተ መቅደስ ኼደች፡፡ በቤተ መቅደስ ተቀምጣ፡ ሐርና ወርቁን እያስማማች ስትፈትል፡ አሁንም እንደገና፡ "ትፀንሲ!" ማለትም፡ "ትፀንሻለሽ!" አላት፡፡

ይህም መልአክ፡ ይህ ነገር ከመኾኑ፡ ከስድስት ወራት በፊት፡ ካህኑ ዘካርያስ፡ በቤተ መቅደስ እያገለገለ ሳለ፡ ሚስቱ ኤልሣቤጥ፡ መጥምቁ ዮሐንስን የምትፀንስ ስለመኾኗ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣለትን መልእክት ያበሠረው፥ ዘካርያስም፡ ይህን ምሥራች ሲነግረው፡ ቃሉን በመጠራጠሩ፡ "**ይህችን ምሥራች እንድነግርህ የተላክሁት፡ እኔ፡ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው፡ ገብርኤል ነኝ!**" ያለው፡ ሊቀ መላእክት ነው፡፡ ይኸው መልአክ፡ ይህን ምሥራች፡ ለዘካርያስ ነግሮት፡ ኤልሣቤጥ ከፀነሰች፡ ከስድስት ወራት በኋላ፡ በዚች ዕለት ደግሞ፡ ለድንግል ማርያም፡ በቤተ መቅደስ ተገልጦላት፡ በሦስተኛው ጊዜ፡ እንዲህ ሲል አበሠራት፡-

"**እነሆ ትፀንሻለሽ፤ ወንድ ልጅንም ትወልጃለሽ፤ ስሙንም፡ 'ኢየሱስ' ትዪዋለሽ፤ እርሱ፡ ታላቅ ይኾናል፤ 'የልዑል ልጅ'ም ይባላል፤ እግዚአብሔር አምላክም፡ የአባቱን፡ የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤ በያዕቆብ ቤትም ላይ፡ ለዘለዓለም ይነግሣል፤ ለመንግሥቱ፡ መጨረሻ የለውም፡፡**"

በዚህ የምሥራቹ ቃል፡ እግዚአብሔር አምላክ፡ ከእርሷ፡ ሰው ኾኖ የመወለዱን ምሥጢር፡ ከእግዚአብሔር መንግሥት ምንነት ጋር አብራርቶ አሳወቃት።

በዚህ ጊዜ፡ እርሷም፡ **"ወንድ ስለማላውቅ፡ ይህ እንዴት! እንዴት ሊኾንልኝ ይችላል?"** ብላ መልሳ፡ በልቧ ያለውን የእውነት ጥያቄ አቀረበችለት። ድንግል ማርያም፡ ይህን ጥያቄ፡ ለመልአኩ ማቅረቧ፡ ተጠራጥራው አይደለም፤ "እኔ፡ ይህን ነገር፡ እንኳን ሳደርገው፡ ስለማላስበውም፡ እንደምን ሊኾን ይችላል?" ስትለው ነው።

መልአኩም፡ **"መንፈስ ቅዱስ፡ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፤ ስለዚህ ደግሞ፡ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ፡ 'የእግዚአብሔር ልጅ' ይባላል፤ እነሆም፡ ዘመድሽ ኤልሣቤጥ፡ እርሷ ደግሞ፡ በእርጅናዋ፡ ወንድ ልጅን ፀንሳለች፤ 'መካን' ትባል ለነበረችው፡ ለእርሷ፡ ይህ፡ ስድስተኛ ወር ነው፤ "ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና!"** የሚለውን፡ ሌላ ጥያቄ ሊያስከትል የማይችለውን አጥጋቢ ምላሽ ሰጣት።

እርሷም፡ ከዚያ በኋላ፡ ወዲያ ወዲህ የማያሰኘውን፡ ይህን፡ መልአካዊ መልስ ስላገኘች፡ አፍአዊውና ውሳጣዊው ኹለንተናዋ ረክቶ፡ ወዲያው፡ **"እነሆኝ የእግዚአብሔር ባርያ! እንደቃልህ ይኹንልኝ!"** ብላ፡ መለኮታዊዉን መልእክት ለመቀበል፡ ፍጹም ዝግጁነቷንና ቁርጥ ፈቃደኛነቷን፡ ለሰማያዊው መልእክተኛ አሳወቀችው። ልክ፡ በዚች ዕለት፥ ከዕለቷም፡ ይህን ቃሏን፡ ከልቦናዋ አፍልቃ፥ በአንደበቷ ባሰማችባት፡ በዚያች ቅጽበት፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ በማሕፀኗ ተፀነሰ።

ስለዚህ፡ **ፈጣሪ፡ ፈቃዱ ኾኖ፡ እንደተስፋ ቃሉ፡ አምላካዊ አካሉንና ባሕርዩን፡ በንጽሕት ድንግል ማሕፀን ውስጥ፡ ከፍጡሩ፡ ሰብኣዊ አካልና ባሕርይ ጋር አዋሕዶ፥ ማለትም፡ ከነፍሷ፡ ነፍስን፥ ከሥጋዋም፡ ሥጋን ነሥቶ፡ በፍጹም ሰውነት የተፀነሰባት፡ ይህች ዕለት፡ "ዕለተ ትስብእት"** ተብላለች።

"ዕለተ ትስብእት" የተባለችው፡ ይህችው፡ ታኅሣሥ ፳ ቀን፡ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ በማሕፀኗ ተቀርጾና ሰው ኾኖ፡ ከእርሷ የሚወለድ የመኾኑን ምሥራች፡ ከእግዚአብሔር አብ ተልኮ፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም ያሰማባት ዕለት ስለኾነች፡ "ብሥራተ ገብርኤል" ተብላም፡ በታላቅ ክብርና ሐሴት ትዘከራለች፤ ትከበራለች። በግእዝ፡ "ብሥራት"፡ "ምሥራች" ማለት ነው። (ሉቃ. ፩፥ ፲፱፤ ፳፮፤ ፴፩-፴፰። ኢሳ. ፯፥ ፲፬፤ ማቴ. ፩፥ ፳፪-፳፫።)

## ፅንሰታ ለማርያም።

የቅድስት ድንግል ማርያም፡ አረጋውያን ወላጆች፡ ኢያቄምና ሐና፡ መካኖች በመኾናቸው፡ ፈጣሪያቸው እግዚአብሔር፡ ልጅ እንዲሰጣቸው፡ በሃይማኖት ተስፋ ጸንተው፥ በጾም፥ በጸሎትና በምጽዋት ምግባራትም ተወስነው ከኖሩ በኋላ፡ የለመኑትን የማይነሣው፥ የነገሩትንም የማይረሳው፡ ይኸው አምላካቸው፡ በሃይማኖታዊ ምግባራቸው፡ ለፍጹምነት የበቃውን ልመናቸውን ተቀብሎ፡ የሐናን ማሕፀን፡ ለአምላክ እናትነት የተመረጠችውን፡ ድንግል ማርያምን ይፀንስ ዘንድ፡ በቅድስናው ከፈተ!

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመፀነሱ፡ ከ፲፮ (አሥራ ስድስት) ዓመታት በፊት፡ በታኅሣሥ ፯ ቀን፡ እመቤታችን ተፀነሰች፤ ያችም ዕለት፡ "ፅንሰታ ለማርያም" ተባለች፡፡

ዕፁብ ድንቅ መለኮታዊ ሥራ ስለኾነው፡ ስለቅድስት ድንግል ማርያም ፅንሰት፡ በትውፊት ያገኘነው ዝክረ ነገር፡ እንዲህ ይላል፡- የእመቤታችን፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የምዝላቶቿ፡ ምዝላቶች ከኾኑት፡ ከኢትዮጵያውያኑ የተገኙት፡ ቅድመ ቅድም አያቶቿ፡ በጥሪቃና ቴክታ ይባላሉ፡፡ ይህ ቀራቸው የማይባሉ፡ ባለጸጎች ነበሩ፡፡

ሀብታቸውም፡ በወርቅና በብር ሚዛን፥ በቀንድና በጋማ ከብት መጠን ብቻ የሚወሰን ሳይኾን፡ በወንድና በሴት አገልጋዮችና ሠራተኞች ብዛትም ጭምር የሚለካ ነበር፤ አንዱን ዓይነት፡ በምሳሌነት ለመጥቀስ፡ ከብዛቱ የተነሣ፡ ወርቁን፡ እንደአምባርና እንደቀለበት እያሠሩ፡ ከበሬውና ከላሙ ቀንድ ላይ ያጠልቁት ስለነበር፡ የወርቁም፥ የከብቱም ብዛት፡ ይህን ያህል፡ "አቅርንተ ወርቅ" (የወርቅ ቀንዶች)፥ ይህን ያህል፡ "አቅርንተ ብሩር" (የብር ቀንዶች) ተብሎ ይቈጠር ነበር እንጂ፡ የቀረው አይቈጠርም ነበር፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን፡ በጥሪቃ፡ ገንዘባቸው ከሚገኝበት ግምጃ ቤቱ ገብቶ፡ የገንዘቡን ብዛት ከተመለካከተ በኋላ፡ ሚስቱን፡ "ቴክታ! እኔ መኻን! አንቺ መኻን! ይህ ኹሉ ገንዘብ ለማን ይኾናል?" አላት፡፡ እርሷም፡ "እግዚአብሔር እንጂ፡ ከእኔ ባይሰጥህ፥ ወይ፡ ከሌላ ይሰጥህ ይኾናልና፡ ለምን አግብተህ፡ አትወልድም?" አለችው፡፡ "ይህንስ እንዳላደርገው፡ የአባቶቻችንና የእናቶቻችን አምላክ ያውቃል!" አላት፡፡

እርሱም፡ ይህን ያላት፡ ያለምክንያት አልነበረም፤ እኒህ ባልና ሚስት፡ ኹለቱም፡ በኢትዮጵያዊነታቸው የሚኖሩበት ሥርዓት፡ ከአንድ በላይ ሚስቶችን ማግባት እንደሚፈቅደውና የእስራኤልን ሕዝብ እንደሚጨምረው፡ እንደሌሎቹ የአረማውያንና አሕዛብ ልማድ ሳይኾን፡ እግዚአብሔር፡ በአዳምና ሔዋን የመሠረተው፥ አንድ ወንድ፡ በአንዲት ሴት፥ አንዲት ሴት፥ በአንድ ወንድ እንዲጸኑ፡ የሚወስነው፡ የጋብቻ ቃል ኪዳን የሚጠበቅበት በመኾኑ ነው፡፡

በዚህ ጊዜ፡ ኹለቱም ስላዘኑበት፡ ስለዚሁ ችግራቸው፡ ወደሚያመልኩት ፈጣሪያቸው ለማመልከት ተስማምተው፡ በየራሳቸው፡ ሱባኤ ገቡ፡፡ ወዲያው፡ ከሌሊቱ በአንዱ፡ ኹለቱም፡ ራእይ አይተዋል፤ ራእዩም፡ እንዲህ የሚል ነበረ፡- "ነጭ እንቦሳ፡ ከበረታቸው ስትወጣ፥ እንቦሳዪቱ፡ እንቦሳን እየወለደች፡ እስከስድስት ስትደርስ፥ ስድስተኛዪቱ፡ ጨረቃን፥ ጨረቃ፡ ፀሓይን ስትወልድ አይተው፡ ወደመፈክረ ሕልም (ሕልም ፈቺ) ኼደው ነገሩት፡፡ እርሱም፡ "ደግ ልጅን ትወልዳላችሁ! ከዚያም፡ እስከስድስት ትውልድ፡ እንደእርሷ፡ ደጋግ የኾኑ የልጅ ልጆችን ታገኛላችሁ! ስድስተኛዪቱ ጨረቃ፡ ከፍጡራን በላይ የምትኾን ልጅን ትወልዳላችሁ! የሰባተኛዋ፡ የፀሓይ ነገር፡ ግን፡ አልተገለጸልኝም፤ እንደነቢይ፥ እንደንጉሥ ያለ፡ ይኾናል!" አላቸው፡፡ እነርሱም፡ "ጊዜ ይተርጉመው!" ብለውት፡ ወደቤታቸው ተመለሱ፡፡

ከዚህ በኋላ፡ እግዚአብሔር፡ የባልና ሚስቱን፡ የኀዘን ጸሎት ሰማ፤ እነሆ፡ ቴክታ ጸነሰች! ሴት ልጅንም ወለደች! "ምኞቴ ተፈጸመልኝ! ስእለቴም ደረሰልኝ!" ስትል፡ ለዚህች የስእለት ልጇ፡ "ሄኤሜን" የሚል ስም አወጣችላት። "ሄኤሜን"ም፡ ሴት ልጅን ወለደች፤ ይህች ልጇም፡ የልጅ ልጅ አይታ፡ ያች የወለደቻት ልጅ፡ "ሄርሜላ" ተብላ፡ እርሷ ደግሞ፡ የእመቤታችንን እናት፡ "ሐናን" ወለደች።

ሐና፡ አካለ መጠን ስታደርስ፡ ከቤተ ይሁዳ ለተወለደ፡ "ኢያቄም" ለሚባል፡ ደግ ሰው አጋቧት። ምክንያት፡ የምዝላቶቿ ምዝላቶች ከኾኑት፡ ቅድመ አያቶቿ ወርዶ፡ እርሷ ላይ ሲደርስ፡ እንደእነርሱ መኻን ኾነች፤ ከዚያውም ጋር፡ በሀብቱ ቦታ፡ ድህነቱ ተተክቷል። ይህንም፡ ከዚህ የሚከተለው ዝክረ ነገር ያረጋግጣል።

የደህነታቸው መጠን፡ ወደምን ዓይነቱ ዝቅተኛ ደረጃ እንደወረደ የሚያሳየው፡ ሐና፡ ወደውጭ ለብሳ የምትኼደው ልብስ እስከማጣት መድረሷ ነበር፤ ለመሳለምና የተለመደ ጸሎቷን ለማድረስ እንኳ፡ ወደእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ለመኼድ ካልቻለችበት ችግር ላይ ወድቃ ነበር።

በእንደዚህ ያለ ኹኔታ ላይ ሣለች፡ ከዕለታት አንድ ቀን፡ የምትወድደው በዓሏ የኾነውን ቀን ለማክበር ይኹን፥ ወይም፡ በልቡናዋ ያለውን ምኞቷን ይፈጽምላት ዘንድ፡ ስእለቷን ለአምላኳ ልታቀርብ፥ ወይም፡ በሌላ፡ ባልታወቀ፡ የሚገፋፋ ምክንያት፡ በግድ ወደእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ለመኼድ ፈልጋ ተነሣች፤ ነገር ግን፡ ለዚያ ልዩ ቀን የሚኾን ማለፊያ ልብስ ስላልነበራት፥ ይህም ማጣቷ፡ ከዚያ ካሰበችው ዓላማዋ፡ ሊያስቀራት የሚችል ምክንያት ኾኖ ስላገኘችው፡ እጅግ አዘነች።

ይህን ችግርዋን ለማስወገድ ስለምትችልበት መንገድ፡ ኀዘን በተመላ ልቡናዋ ተክዛ፡ ስታወጣና ስታወርድ ሣለች፡ በዝሙት የምትኖር፡ አንዲት ጎረቤቷ አይታት ኖሮ፡ "ሐና! ዛሬ ምን ኾነሻል? በከባድ ኀዘን ተክዘሻል፤ ምነው?" አለቻት።

ሐና፡ ለዚህ፡ ለጎረቤቷ ጥያቄ፡ መልስ ለመስጠት፡ የመጣላት መፍትሔ አንድ ብቻ ኾኖ አገኘችው፤ እርሱም፡ ይህንኑ ችግሩዋን፡ ለዚችው ጎረቤቷ ማዋየት ነበር። እርሷም፡ በዚሁ አሳቧ ቆርጣ፡ እንዲህ ስትል፡ ችግሩዋን፡ ለዚያችው ጎረቤቷ አዋየቻት፡- "ዛሬ፡ ወደቤተ መቅደስ ኼጄ፡ እሳለማለሁ ብዬ አስቤ ነበር፤ ነገር ግን፡ ለብሼው የምኼደው ልብስ ስለሌለኝ፡ የምችል አልመሰለኝም፤ ለዚህ ነው።"

ያች ጎረቤቷም፡ "ልብስማ፡ የእኔ፡ ከአንድ፥ ኹለት፥ ሦስት አለልሽ አይደለምን? ለምን፡ ከእነዚያ፡ አንዱን መርጠሽ፡ ያን ለብሰሽ፡ አትኼጂም?" አለቻት።

ሐናም፡ በቅን ኅሊና፥ በየዋህ ልቡናና በትሑት ሰብእና፡ "አይ! ያማ አይኾንም! ያቺ ልብስኮ የተሰበሰበው፡ በዐስበ ደነስ (በኃጢአት ዋጋ)፥ በዐስበ ዝሙት (በዝሙት ዋጋ) ነው፤ እግዚአብሔር ደግሞ፡ ንጹሓ ባሕርይ ነውና፡ ንጹሕ ነገርን ይወድዳል፤ ይህን፡ ያንቺን ልብስ ለብሼ ብለምነው፡ 'እንዴት ይሰማኛል' ብዬ ነዋ!" አለቻት።

ሴቲቱም፡ “ሐና! እኔ፡ 'በምን ምክንያት፡ ልጅ ነሣት?' እያልሁ፡ ሳዝንልሽ እኖር ነበር፤ ለካ፡ እንዲህ፡ እንደደንጊያ አድርቆ ያስቀረሽ፡ ይህ ክፋትሽ ኖርዋልና!” አለቻት።

ሐናም፡ በዚህ፡ እጅግ አዘነች።

ይህን ኀዘኗን የሚያባብስ፡ ሌላ ድርጊት ደግሞ፡ አጋጠማት፤ ይህም፡ ካላሰበችው አግጣጫ የተሠነዘረ ነበር። ሐና፡ ያላትን፡ ያንኑ ልብሷን አጽድታ፡ ከባሏ ከኢያቄም ጋር፡ ኹለቱም ኹሉ፡ “ለእግዚአብሔር፡ መሥዋዕት እናቀርባለን!” ብለው፡ ወደቤተ መቅደስ ኼዱ፤ ሊቀ ካህናቱ፡ “ሮቤል” ይባላል። እርሱም፡ “እናንተማ፡ 'ብዙ! ተባዙ!' ብሎ፡ እግዚአብሔር፡ ለአዳም የነገረውን፡ የበረከት ቃል ያስቀረባችሁ፡ ርጉማን አይደላችሁምን? ቢጠላችሁ ነው እንጂ፡ ቢወድዳችሁማ፡ ልጅን ይሰጣችሁ አልነበረምን? ስለዚህ፡ መሥዋዕታችሁን አልቀበልም!” ብሏቸዋል። ከዚህ በቀር፡ የእስራኤል ሽማግሎች የኾኑ ወላጆች ብቻ የሚመገቡት፡ ተረፈ መሥዋዕት (ከመሥዋዕቱ የሚተርፍ) ነበር፤ ያንንም እንዳይሳተፉ፡ ይኸው ሊቀ ካህናት ከልክሏቸዋል። በዚህ ኹሉ፡ ተደራራቢ ኀዘን ደርሶባቸው፡ በትካዜ ኾነው፡ ወደቤታቸው ተመለሱ።

ከቤተ መቅደስ ሲመለሱ፡ በመንገዳቸው ላይ፡ እንዲህ፡ በኀዘን በትካዜ ተውጠው፡ ከዛፍ ጥላ ሥር፡ ዐረፍ ብለው ሣሉ፡ ሐና፡ ርግቦች፡ ከልጆቻቸው ጋር የሚያደርጉትን ጨዋታ፥ ዛፎችም፡ አብበውና አፍርተው፡ የሚያሳዩትን፡ የሥነ ፍጥረት ውበት ተመልክታ፡ “አቤቱ! ርግቦችን፡ በባሕርያቸው እንዲዋለዱ፥ ዕፀዋትንም፡ በተፈጥሮአቸው እንዲያብቡ፡ እንዲያፈሩ የምታደርግ አምላክ፡ የእኔ ምንነቱ፡ ከደንጊያ የተሠራ ይመስል፡ ልጅ የነሣኸኝ፡ ለምን ይኾን?” ብላ አዘነች።

ኹለቱም፡ ከቤታቸው ሲገቡ፡ ተነጋገሩና፡ “ወንድ ልጅ ብንወልድ፡ 'ወጥቶ ወርዶ፥ አርሶ ቆፍሮ፡ ይርዳን!' አንልም፤ ለቤተ እግዚአብሔር፡ አንጣፊ፥ ጋራጅ ኾኖ ይኖራል፤ ሴት ብንወልድ፡ 'ዕንጨት ሠብራ፥ ውኃ ቀድታ ትርዳን!' አንልም፤ ለቤተ እግዚአብሔር፡ መሶበ ወርቅ ሰፍታ፥ መጋረጃ ፈትላ ትኑር!” ብለው፡ ብፅዓት ገቡ።

ኢያቄምና ሐና፡ ከቀደሙት አያት ቅድመ አያቶቻቸው ራእይ የረቀቀ፡ ሌላ ራእይ፡ በየበኩላቸው ያያሉ፤ ይህም የኾነው፡ የሐምሌ አመ ፴ (የወሩ ማብቂያ) ዕለት ነበር። በዚች ዕለት ሌሊት፡ እርሷ፡ ለእርሱ፡ “ፀምር ሲያስታጥቁህ (ከበግ ፀጕር የተሠራ ማለፊያ ልብስ፡ ማለትም፡ በርኖስ ሲያለብሱህ)፤ መቋሚያህ አፍርታ፥ ፍጥረት ኹሉ ሲመገባት አየሁ!” ብላ፥ እርሱ ደግሞ ለእርሷ፡ “ነጭ ርግብ፡ ሰባቱን ሰማያት ሠንጥቃ መጥታ፡ በራስሽ ላይ ስታርፍ፤ በቀኝ ጆሮሽ ገብታ፡ በማሕፀንሽ ስታድር አየሁ!” ብሎ፡ ኹለቱም፡ ያዩትን ራእይ ተጨዋውተዋል። ወደሕልም ፈቺም ኼደው፡ እንዲተረጕምላቸው ቢነግሩት፡ “ደግ ልጅ ትወልዳላችሁ!” ከማለት በቀር፡ አስተካክሎና አሟልቶ ሊፈታላቸው አልቻለም። እነርሱም፡ “አንተስ አልፈታኸውም፤ ጊዜ ይፍታው!” ብለው፡ ወደቤታቸው ተመለሱ።

እነርሱም፡ የራእያቸውን ፍጻሜ፡ በሃይማኖት ተስፋና በትዕግሥት ምግባር፡ እየተጠባበቁ ሣሉ፡ የእግዚአብሔር መልአክ መጥቶ፡ “ደግ ልጅ ትወልዳላችሁ!” ብሏቸው፡ እመቤታችን ድንግል ማርያም፡ በብሥራተ መልአክ፡ በፈቃደ አምላክ፡ ታኅሣሥ ፯ ቀን ተፀነሰች። በተፀነሰችም ጊዜ፡ ብዙ ታምራት ተደርጓል። ከእነዚህም መካከል፡ ጥቂቶቹን፡ እዚህ ላይ እንጠቅሳቸዋለን፦

ለሐና፡ "ቤርሴባ" የምትባል አክስት ነበረቻት፤ አንድ ዓይና ነች፤ "ሐና! እግዚአብሔር፡ በረድኤት ጐበኘሽ መሰለኝ! ጡትሽ፡ ጠቁርዋል፤ ከንፈርሽም፡ አርሩዋል፤" ብላ ማሕፀኗን ዳስሳ፡ ዓይኗን ብታሽው፡ በርቶላታል። ይህን፡ አብነት አድርገው፡ ሕሙማን ኹሉ፡ የሐናን ማሕፀን እየዳሰሱ፡ የሚፈወሱ ኾነዋል።

ደግመኛም፡ "ሳምንስ" የሚባል፡ ያጎቷ ልጅ ነበር፤ ሞተ፤ ሐና፡ ትወድደው ነበርና፡ ያልጋውን ሸንኰር ይዛ፡ እየዞረች ስታለቅስ፡ ጥላዋ ቢያርፍበት፡ ተነሥቶ፡ "የሰማይና የምድር ፈጣሪ እያት ሆይ! ሰላም ለአንቺ ይኹን!" ብሎ፡ ከዚያ የሕልም ፈቺ የቀረውን ተርጕሞላታል።

## በኣታ ለማርያም።

ሕፃን ማርያም፡ በቅዱሳን ወላጆቿ ስእለት፡ እግዚአብሔርን ልታገለግል የተሰጠች፡ የብፅዓት ልጅ ስለኾነች፡ እንደኦሪቱ ሥርዓት፡ የእናቷን ማኅፀን፡ በብኵርናዋ በመክፈት፡ በተወለደች፡ በ፹ ቀኗ፡ በኅዳር ፳፩ ቀን፡ በወላጆቿ ዕቅፍ፡ በእግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ፡ ወደቤተ መቅደስ ከገባችበት ሥርዓት ቀጥሎ፡ በሦስት ዓመቷ፡ ለኹለተኛ ጊዜ፡ እንደገና፡ ወደቤተ መቅደስ ገብታ፡ በዚያ፡ የ፲፪ ዓመታት ኑሮዋን የጀመረችበት፡ ታኅሣሥ ፫ ቀን፡ "በኣታ ለማርያም" ተብሎ የሚከበር ኾኗል።

በዚህ በዓል ዕለት ሊታሰብና ሊነገር የሚገባው፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የዜና መዋዕሏ የመጀመሪያ ክፍል፡ እንዲህ ነው፡-

ሕፃን ማርያም፡ በተወለደች፡ በሦስት ዓመቷ፡ እናቷ ሐና፡ ባሏን ኢያቄምን፡ "ይህች ብላቴና፡ ሆዷ፡ ዘመድ ሳይወድድ፥ አፏም፡ እህል ሳይለምድ፡ ለእግዚአብሔር በገባነው ቃል መሠረት፡ ወስደን፡ ለቤተ መቅደስ አንሰጣትምን? 'የሰጠ ቢነሣ፡ የለበት ወቀሳ!' እንዲሉ፡ አንዳች ነገር ብትኾንብን፡ ከልጃችንም፥ ከእግዚአብሔርም ሳንኾን እንዳንቀር!" አለችው።

እርሱም፡ "የእናትነት ፍቅርሽ ይለቅልሽ ብዬ ነው እንጂ፡ እኔማ፡ ፈቃዴ አይደለምን?" አላት። ከፍቅሩዋ ጽናት የተነሣ፡ ሐና፡ ሕፃን ማርያምን፡ ከጭኑዋ አውርዳት አታውቅም ነበር። ምክንያቱም፡ አንድ ቀን፡ ብቻዋን፡ ከቤት ውስጥ ትታት፡ ከደጅ ወጥታ ብትመለስ፡ የእግዚአብሔር መልአክ ሠውሮባት፡ ጥሩ፡ ግራ አግኝታት ስለነበረ ነው፤ ከዚያ በኋላ፡ ያው እየመሰላት፡ ተለይታት አታውቅም።

ወላጆቿ፡ ይህን ተነጋግረው እንዳበቁ፡ ሕፃን ልጃቸውን፡ ማርያምን ወስደው፡ ለቤተ መቅደስ ሰጧት። በዚያን ጊዜ የነበረው ሊቀ ካህናት፡ "ዘካርያስ" ይባላል፤ እርሱም፡ ስለምግቧ ነገር ሊያስወስን፡ መጥቅዕ (ደወል) ደውሎ፡ ሕዝቡን ሰብስቦ፡ እየተወያዩ ሣሉ፡ የእግዚአብሔር መልአክ፡ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ፋኑኤል፡ የሰማይ ኅብስትና የሰማይ ጽዋ ይዞ፡ ከሰማይ ወርዶ፥ ረብቦ ታየ፤ በዚህ ጊዜ፡ ሊቀ ካህናቱ ዘካርያስ፡ ለእርሱ የወረደለት ሀብት መስሎት፡ ሊቀበል ቢነሣ፡ ወደላይ ራቀበት፤ የሊቀ ካህናቱ ተወራጅ፡ "ስምዖን" ይባላል፤ እርሱም፡ ለመቀበል ቢነሣ፡ ወደላይ ራቀበት።

ከዚህ በኋላ፡ “ጥበበ እግዚአብሔር፡ ምሥጢሩ አይመረመርምና፡ ምናልባት፡ ለዚህች ብላቴና የመጣ ሀብት እንደኾነ፡ ማን ያውቃል? እስኪ እንየው!?” ብለው፡ ለብቻዋ አድርገዋት፡ ፈቀቅ ቢሉ፡ ድንኰል፥ ድንኰል እያለች፡ እናቷን ስትከተል፡ መልአኩ፡ ፈጥኖ ወርዶ፡ አንድ ክንፉን፡ አንጥፎ፥ አንድ ክንፉን ደግሞ፡ ጋርዶ፡ በሰው ቁመት ያህል፡ ከምድር አስለቅቆ፥ ከፍ አድርጓትና መግቧት ዐረገ፡፡

በዚህ ጊዜና ከዚህ የተነሣ፡ ካህናቱና ሕዝቡ፡ “የምግቧ ነገር፡ እንዲህ ከተያዘልንማ፡ ከሰው ጋራ ምን ያጋፋታል?” ብለው፡ ሕፃን ማርያምን፡ ከወላጆቿ ተቀብለው፡ ወደቤተ መቅደስ አግብተዋት፡ በዚያ፡ አሥራ ኹለት ዓመት ኖራለች፡፡ (ከቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ፡፡)

## የታኅሣሥ ገብርኤል፡፡

በዚሁ በታኅሣሥ ወር፥ በ፲፱ነኛው ቀን የሚውለው፡ የ“ታኅሣሥ ገብርኤል” በዓል፡ የሚከበርበት ምክንያት እንዲህ ነው፡-

እግዚአብሔር፡ በሙሴ መሪነት፡ የእሥራኤል ሕዝብ፡ በግብፅ አገር፡ ይገኙበት ከነበረው የባርነት አገዛዝ፡ ነጻ አውጥቶ፡ ቤተ መቅደሳቸውንና ከተማቸውን፡ በኢየሩሳሌም አድርገው፡ በምድረ ከነዓን እንዲኖሩ አበቃቸው፡፡ እነርሱ ግን፡ ባካባቢያቸው ያሉትን አሕዛብ እየተከተሉ፡ አምልኮ ባዕድ በመፈጸም፡ አምላካቸውን እግዚአብሔርን አሳዘኑት፡፡ በነቢያቱ፡ ቢመክራቸውና ቢገሥፃቸውም፡ በዚያ ኃጢኣታቸው እየጨመሩበት ከመኼድ በቀር፡ ከበደላቸው ተጸጽተው ሊመለሱ፡ ጨርሶ የማይቻል ኾነ፡፡

በዚህ መልክ፡ በፈጣሪያቸውና ከእርሱ ጋር በተጋቡት ቃል ኪዳናቸው ላይ፡ በሥውርና በገሃድ ያካኺዱት የነበረው ክህደት፥ ዓመፅና ኣመንዝራነት፡ በመጨረሻ፡ ጽዋው ስለሞላ፡ እግዚአብሔር፡ ለዚህ ድርጊታቸው፡ ምስክር የኾነችውን ታቦተ ጽዮንን፡ ከእስራኤላዊው ንጉሥ፡ ከሰሎሞንና ከኢትዮጵያዊቷ ንግሥት፡ ከማክዳ በተወለደው፡ በቀዳማዊ ምኒልክ አማካይነት፡ በቅድሚያ፡ ወደኢትዮጵያ እንድትኼድ አደረገ፡፡ ከዚያ በኋላም፡ ያወረሳቸውን አገርና ከተማ፡ ወርሮ ይበዘብዝ ዘንድ፡ አረማዊውን ንጉሥ፡ ናቡከደነፆርን፡ ታላቅ የሠይፍ ኃይልን አስታጥቆ፡ ወደኢየሩሳሌም ላከ፤ እርሱም፡ በዚያ፡ የቅጣት ተልእኮውን እንዲፈጽም፥ ኃጢኣተኛውንም የእስራኤል ትውልድ ፈጅቶ፡ የተረፉትን፡ በምርኮ፡ ወደምድሩ፡ ወደባቢሎን እንዲወስዳቸው፥ ለስደትም እንዲዳርጋቸው፡ አሠለጠነው፡፡

ለዚያ ስደት ከተዳረጉት እስራኤላውያን መካከል፡ በሃይማኖታቸው የጸኑና በምግባራቸው የተጠናከሩ፡ አካኼዳቸው፡ ከነቢዩ ዳንኤል ጋር የኾነ፡ አናንያ፥ አዛርያና ሚሳኤል የተባሉ መንፈሳውያን ወጣቶች ነበሩ፡፡ እነዚህ፡ “ሠለስቱ ደቂቅ” የተባሉት፡ ሦስት ጐልማሶች፡ በእውቀታቸውና በብልህነታቸው ተመርጠው፡ የንጉሡ ሹማምንት ኾነው ያገለግሉ ነበር፡፡

የኋላ ኋላ ግን፡ የሃይማኖትና የሥልጣን ባላጋራዎቻቸው ባውጠነጠኑትና እስከንጉሡ በደረሰው ሴራ፡ የአገሩን አማልክት እንዲያመልኩ፥ ንጉሡ ላቆመውም ጣዖት እንዲሰግዱ፥ ያን ባያደርጉ፡ በአዋጅና ባደባባይ እየነደደ ባለ፡ አስፈሪ የእሳት ነበልባል ውስጥ የሚጣሉ መኾናቸውን የሚገልጽ፡ የፈተና ጥያቄ፡ ከንጉሡ ቀረበላቸው:: እነርሱም፡ ለገንዘብና ለሹመት ጓጉተው፥ የንጉሡን ቍጣም ፈርተው፡ አምላካቸውን የማይክዱ፥ ሃይማኖታቸውንም የማይለውጡ መኾናቸውን በመግለጽ፡ " **ንጉሥ ሆይ! የምናመልከው አምላካችን ፡ ከእጅህም ኾነ፡ ከዚህ፡ ከሚነድደው የእሳት ነበልባል፡ ሊያድነን ይቻለዋል፤ ባያድነንም እንኳ፡ አማልክትህን እንዳናመልክ፥ ላቆምኸውም፡ ለወርቁ ጣዖት እንዳንሰግድለት እወቅ!**" ሲሉ፡ በድፍረትና በቆራጥነት መልስ ሰጡት::

በዚህ ጊዜ፡ ፍርዱ እንዲፈጸምባቸው፡ ከንጉሡ ታዝዞ፡ ሦስቱም ገድለኞች፡ በሚነድደው እሳት ውስጥ ተጣሉ:: ወደእሳቱ ሊጥሏቸው የወሰዷቸው ኃያላንም፡ በነበልባሉ ብርቱ ወላፈን እየተቃጠሉ ሞቱ::

ወደእሳቱ ውስጥ ታሥረው የተጣሉት፡ እኒህ መንፈሳውያን አርበኞች ግን፡ የእግዚአብሔር መልአክ፡ እሳቱን አቀዝቅዞላቸው፡ በነበልባሉ መካከል፡ ወዲያ ወዲህ ሲመላለሱ ከመታየት በቀር፡ በአካላቸው ቀርቶ፡ በልብሳቸው ላይ እንኳ፡ አንዳችም ጉዳት ሳይደርስባቸው፡ ከተፈረደባቸው የቃጠሎ ሞት ድነው፡ በደኅና ሊወጡ ችለዋል:: ይህንም፡ "**የዚያን ጊዜም፡ ንጉሡ ናቡከደነፆር፡ ተደነቀ፤ ፈጥኖም ተነሣ፤ አማካሪዎቹንም፡ 'ሦስት ሰዎችን አሥረን፡ በእሳት ውስጥ ጥለን አልነበረምን? ...እነሆ፡ እኔ፡ የተፈቱ፥ በእሳቱም መካከል የሚመላለሱ፡ አራት ሰዎችን አያለሁ፤ ምንም አላቈሰላቸውም፤ የአራተኛውም መልክ፡ የአማልክትን ልጅ ይመስላል፤' ብሎ መለሰ::**" የሚለው፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ያረጋግጣል::

"**የአራተኛው መልክ፡ የአማልክትን ልጅ ይመስላል፤**" የተባለው፡ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል መኾኑን፡ ከትውፊታችን አግኝተነዋል:: (ዳን. ፫፥ ፳፬-፳፭::)

በሃይማኖት ሳይወላውሉ፡ በምግባር ተጠናክረው፡ እስከመጨረሻው፡ ማለትም፡ የሞት ጽዋን ለመቀበል፡ ተዘጋጅቶና ቀርጦ እስከመቅረብ ድረስ፡ በጀመሩት ገድል፡ ጸንቶ መገኘት፡ የሚያስከትለው ውጤትና የሚያስገኘው ፍሬ፡ በነፍስ ብቻ ሳይኾን፡ የሥጋ ሞትን ጭምር በማስቀረት፡ የምሕረት ሕይወትን፥ በክፉት ኃይላትም ላይ፡ ድልን የሚያቀዳጅ፡ የመላእክትን ተራዳኢነት መኾኑን፡ በዚሁ፡ በታኅሣሥ ፲፱ ቀን የምናከብረው፡ የ"ታኅሣሥ ገብርኤል" በዓል ያስታውሰናል፤ ያስተምረናል::

# ዘመነ ስብከት።

“ዘመነ ስብከት”፡ በታኅሣሥ ፳፰ እና በጥር ፲ ቀኖች መካከል ያሉት አራት፡ የእሑድ ሰንበታት፡ ከነሳምንቶቻቸው፡ እያንዳንዳቸው፡ በቅደም ተከተል፡ “ስብከት”፥ “ብርሃን”፥ “ኖላዌ” እና “ገና” ተብለው የሚጠሩት ናቸው።

በእነዚህ ሰንበታትና ሳምንታት፡-

- እግዚአብሔር ወልድ፡ በመንፈስ ቅዱስ ግብር፡ በድንግል ማርያም ማሕፀን ተፀንሶ፡ በፍጹም ሰውነት፡ ከእርሷ ስለመወለዱ፥
- የሰውነት አመጣጡም፡ ለዓለሙ በደል ቤዛ ኾኖ፡ የመሥዋዕትነት ዋጋን በመክፈል፡ ፍጥረቱን ለማዳን ስለመኾኑ፥
- “ኢየሱስ ክርስቶስ” በተባለበት ስሙም፡ በምድር ላይ እየተመላለሰ፡ ከኃጢኣት በቀር፡ እውነተኛውን ሰውኛ አኗኗር በመኖር፡ ለሰው ልጆች ኹሉ፡ ፍጹም አርአያና አብነት የኾነ ትምህርትን ስለማበርከቱ፥
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመጋቢት ፳፯ ቀን፡ በዕለተ ዓርብ የፈጸመውን ስቅለቱን በማሰብ፡ የሳምንቱን ዓርብና የወሩን ፳፯ኛ ቀናት፡ "መድኃኔ ዓለም!" በሚል ስያሜ፡ ዓመታዊ ብቻ ሳይኾን፡ ሰሙናዊና ወርኃዊ በዓላችን አድርገን፡ በጾምና በጸሎት፥ በማኅሌትና በቅዳሴ እንደምናከብረው ኹሉ፡ ትንሣኤውን ያሳየበትን፡ መጋቢት ፳፱ ቀንና ዕለተ እሑድን ደግሞ፡ እንዲሁ፡ ከእነዚሁ መለኮታውያን ተልእኮዎች ጋር በተያያዘ መልኩ፡ "በዓለ ወልድ" ብለን፡ ዓመታዊዉን ብቻ ሳይኾን፡ የየሳምንቱን እሑድና የየወሩን ፳፱ኛ ቀን ጭምር፡ በበዓልነት ስለማዘከራችን፡ በነቢያት የተነገሩትን፡ የእግዚአብሔርን ትንቢታዊ ቃላት በመጥቀስ፡ ሰፊ ስብከትና ምዕዳን (ምክር) ይሰጥባቸዋል፤ የተስፋ ዝማሬ ይሰማባቸዋል፤ ስለሥጋዌ ምሥጢርም፡ የቅኔያት ማዕበል ይወርድባቸዋል።

እነዚህን አርእስት በመከተል፡ በእነዚሁ ሳምንታት፡ “**ፈኑ እዴከ እምአርያም!...ፈኑ ብርሃነከ ወጽድቀከ...**”፡ ማለትም፡ “**እጅህን፡ ከሰማይ ላክ! ...ብርሃንህንና እውነትህን ላክ!**” እያሉ፡ የቀደሙት ሰዎች፡ ወደፈጣሪያቸው ያቀርቡት የነበረው ያልተቋረጠ ልመናቸው ተሰምቶላቸው፡ “**አነ ውእቱ፡ ኖላዌ ኄር!**” ማለትም፡ “**ቸር ጠባቂ፡ እኔ ነኝ!**” የሚላቸውና “**የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ**”፥ “**እውነተኛው የዓለም ብርሃን**” የተባለው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እነሆ፡ “**ሰው ኾኖ፡ በድንግል ማሕፀን ተፀነሰ! ተወለደ! እንደሰው፡ በምድር ላይ ተመላለሰ!**” በማለት፡ በመንፈስ፡ ወደኋላ ተመልሰን፡ የነቢያትን የተስፋ ጉዞ፡ በጾምና በጸሎት፥ በዝማሬና በስባሔ እያካኼድን እንፈጽምባቸዋለን። (መዝ. ፻፵፫፥ ፯-፰፤ ፵፪፥ ፫፤ ፸፩፥ ፱-፲። ዮሐ. ፲፥ ፩-፲፯።)

# የጥር ሥላሴ፡፡

ከበዓለ ጥምቀት በፊት፡ ጥቂት ቀደም ብሎ፡ በጥር ፯ ቀን፡ “የጥር ሥላሴ” በዓል ይከበራል፡፡ ይህም የኾነው፡ በታኅሣሥ ፩ ቀን በሚውለው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ትስብእት፡ ማለትም፡ አምላክ ሰው ኾኖ፡ በድንግል ማርያም ማሕፀን በመፀነሱ፡ የእግዚአብሔር፡ የአንድነቱና የሦስትነቱ ምሥጢር ስለተገለጸ፥ ስለታወቀና ስለተረዳ፡ የምሥጢረ ሥላሴና የምሥጢረ ሥጋዌ ነገር፡ በሰፊው እየተነገረ፡ ትምህርቱ እንዲሰጥበት፥ ምሥጢሩም እንዲፍታታበት ታስቦ ነው፡፡

ከዚህ በኋላ፡ “አስተርእዮ”፡ ማለትም፡ “የእግዚአብሔር ሰው ኾኖ የመገለጡ ምሥጢር”፡ በግልጽና በገሃድ፥ በይፋና በአዋጅ የሚነገርበት ወራት ከሚጀምርበት፡ ከጥምቀቱ በዓል እንደርሳለን ፡፡

\+ \+ \+